Monthly Newsletter Vol 17 No. 4

PRINTED BY
International & Public Relations Directorate

DEC 2020

# የኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ

# Ethiopian Civil Service University



## ECSU & EMI Sign MoU

## 15ኛው የብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች በዓል ቀን







## ራዕያችን

የሀገራችንን ልማትና ትራንስፎርሜሽን እውን ለማድረግ ቀልጣፋ፣ ውጤታማ፣ ግልጽና ተጠያቂነት ያለው ፐብሊክ ሰርቪስ ከመገንባት አኳያ በ 2017 በአፍሪካ የልህቀት ማዕከል መሆን

## ተልዕኳችን

ፐብሊክ ሰርቪሱ የአገልጋይነት መንፈስ የተላበሰ እና በግልጽነትና በተጠያቂነት የሚሰራ እንዲሆን አቅሙን በስፔሻላይዝድ ትምህርት፣በስልጠና፣ በማማከር፣በምርምር እና ማህበረሰብ አገልግሎቶች በቀጣይነት መገንባት

## እሴቶቻችን

ተገልጋይ ተኮር
ቁርጠኝነት
ሁሌም መማር
ብዝሀነት መቀበል
ትኩረት ልዩ ድጋፍ ለሚሹ
አሳታፊነት
ተባብሮ መስራት

## Our Vision

To become a leading center of excellence in public service capacity building in Africa by 2025 through building efficient, effective, Transparent and accountable public service which can contribute to the realization of the development and transformation drive of the country

## Our Mission

Enhancing the service orientation, transparency and accountability of the public service by building its capacity through Specialized Education,Training, Consultancy, Research and Community Services.

## Our Values

Customer Focus
Commitment
Continuous Learning
Welcoming Diversity
Attention to the Disadvantaged
Participation
Collaboration

# Ethiopian Civil Service University

## Content


15ኛዉየኢትዮጲያ ብሔር ብሄረሰቦችና ሕዝቦች ቀን በኢሲሰዩ ተከበረ — 1

ECSU & EMI Sign MoU — 3

Research and Community Service Inaugurates Research Resource Center — 4

Mindset Training Given to Community Radio Staff — 5

የ2013 ዓ.ም የትምህርት ዘመን መጀመርን አስመልክቶ በፕሮፌሰር ፍቅሬ ደሳለኝ የተላለፈ መልዕክት — 6

15ኛው የብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች በዓል አከባበር በኢ.ሲ.ሰ.ዩ — 9



**Editor In -Chife**
Tariku Ayano

**Editors**
Anteneh Demisse
Meley Tekeste

**Photos**
Ibsa Bekele
Dereje Tesfaye

**ግራፊክስ እና Layout Design**
Dereje Tesfaye


# የዝግጅት ክፍሉ መልእክት

በዓለማችን ብሎም በሀገራችን በተከሰተው የኮረና ቫይረስ ወረርሽኝ ምክንያት የገጽ ለገጽ የመማር ማስተማር ተግባር ለበርካታ ወራት ተቋርጦ መቆየቱ ይታወቃል፡፡ ነገር ግን የቫይረሱ ስርጭት በአጭር ጊዜ ውስጥ በፍጥነት የመቆጣጠሩ ሁኔታ በቀላሉ የሚታለም ባለመሆኑ በመንግስት በተሰጠው አቅጣጫና በሳይንስና የከፍተኛ ትምህርት ሚኒስቴር ባስቀመጠው ፕሮቶኮል መሰረት የገጽ ለገጽ የመማር ማስተማሩ ተግባር ዳግም የተጀመረ ሲሆን ባለፉት ጊዜያት የባከኑትን ወርቃማ የትምህርት ጊዜያት ከግምት ውስጥ በማስገባትና ያለውን ተጨባጭ ሁኔታ በመገንዘብ በትምህርት መርሀ ግብሩ ላይ የተወሰነ ማሻሻያ ተደርጎአል፡፡

ከዚህ ጋር ተያይዞ በየእለቱ የምናከናዉናቸዉ ተግባራት ቀደም ሲል ከምንሰራዉ ስራ በእጥፍ ማሰብ ፣ማቀድእና መስራት ይጠይቃሉ፡፡ ይህም በቀዉስ ወቅት እንዴት ከቀዉሱ መዉጣትእንደምንችል፣ ቀዉሱን እንዴት መቆጣጠር እንዳለብንና ብዙ ስራ ከኛ እንደሚጠበቅ የሚያመላክት ነዉ፡፡በቀዉሱ የተፈጠረዉን ጫና ተቋቁመን የምንሰራቸዉን ስራዎች ዉጤታማ ለማድረግ ከወትሮዉ በተለየ መልኩ ትልቅ ጥረት ከተቋሙ ሰራተኞች ይጠበቃል፡፡

በመሆኑም ይህን ወቅታዊ የሆነ ችግር በሀገር ደረጃ እስከምናልፈውና ነገሮች ወደነበሩበት ሁኔታ እስኪመለሱ ድረስ መምህራንናሰራተኞች የተፈጠረውን ጫና በመቋቋም ለዩኒቨርሲቲው ተልዕኮ መሳካት ወሳኝ ሚናችሁን እንድትጫወቱ የዝግጅት ክፍሉ መልዕክቱን ለማስተላለፍ ይወዳል፡፡

**ዝግጅት ክፍሉ**

# 15ኛዉ
# የኢትዮጲያ ብሔር ብሄረሰቦችና ሕዝቦች ቀን በኢሲሰዩ ተከበረ

የኢትዮጲያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ ሰራተኛች 15ኛዉን የብሔር ብሄረሰቦችናሕዝቦች ቀን “እኩልነትና ሕብረ-ብሄራዊ አንድነት ለጋራ ብልጽግና” በሚል መሪ ቀል ከ23/3/2013-24/3/2013 ዓ.ም በአባይ አዳራሽ በተለያዩ ዝግጅቶች አከበሩ፡፡



**ፕ/ ር ፍቅሬ ደሳለኝ**
***የኢሲሰዩ ፕሬዚዳንት***



በመክፈቻ ንግግራቸዉ ፕ/ር ፍቅሬ ደሳለኝ የኢትዮጲያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ ፕሬዚዳንት እንደተናገሩት ኢትዮጲያ የምትባል ሀገር የተዋቀረችዉ በብሄር ብሔረሰቦችናህዝቦች ስብስብ ነዉ ፡፡በተለያዩ ጊዚያት የተለያዩ መንግስታት ተለዋዉጠዋል፤ የተለያዩ ችግሮችም አልፈናል ነገር ግን ኢትዮጲያ አንድነቷንናሉአላዊነቷን ጠብቃ ቆየታለች ወደፊትም ትቀጥላለች፡፡ብዝኃነታችንን ደግሞ ለሰላም፣ለልማትና ለሁለንተናዊ ብልፅግና ይበልጥ መጠቀም ይገባናል ብለዋል፡፡እኛ ኢትዮጵያዉያን የቆየውን የአብሮነትና የአንድነት እሴቶች ይበልጥ በማጠናከር የተጀመረውን የለዉጥ ጉዞ ወደ ፊት ማራመድ ከሁሉም ሀገር ወዳድ የሚጠበቅ ነዉ ብለዋል፡፡



የፖለቲካ አስተሳሰብና ልዩነት በጠረጴዛ ዙርያ አለመፍታት ዋጋ እያስከፈለን ይገኛል፤ ስለዚህም እኛ ምሁራን የመፍቴሔ ሀሳብ አመንጪ መሆን አለብን ፡፡ እንደ ተቋም ስንሰራ በየኔነት ስሜት እየሰራን እራሳችንንና ሀገራችንን እንድንጠቅም ልዩነታችንን እንደውበት ለተሻለ አንድነታችን እናዉለዉ ሲሉ አሳስበዋል፡፡ ሰራተኛዉም በሀገራዊ ጉዳዮች የነቃ ተስትፎ እንዲያደርግ በዚህ መድረክም ሀሳቡን በግልጽነት ካለምንም የሀሳብ ቁጠብነት እንዲገልጽ በማሳሰብ የእለቱን ፕሮግራም አስጀምረዋል፡፡

በእለቱ ለዉይይት መነሻ የሚሆኑ ሁለት ጽሁፎች ማለትም አገራዊ ሪፎርም ለጠንካራ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሥርአት ግንባታ(ነጻ፣ገለልተኛናብቃት ያላቸዉ ተቋማት ግንባታ እንደወሳኝ የሪፎርም አጀንደ) እና በወቅታዊ የሀገራዊ ጉዳዮች ዙርያ በዶ/ር አለማየሁ ደበበ የምርምርና ማህበረሰብ ም/ፕሬዚዳንት እና በዶ/ር ዋቃሪ ነጋሪ የስልጠናናማማከር ም/ፕሬዚዳንት ቀርቦአል፡፡





## ዶ/ር አለማየሁ ደበበ
*የምርምርና ማህበረሰብ ም/ፕሬዚዳንት*

## ዶ/ር ዋቅሪ ነገሪ
*የስልጠናና ማማከር ም/ፕሬዚዳንት*

በተጨማሪም በተጠቀሱት ርእሰ ጉዳዮች ዶ/ር ተመስገን ቡርቃ የዩንቨርሲቲዉ ሥራ አመራር ቦርድ ሰብሳቢ እና ፕ/ር ፍቅሬ ደሳለኝ አወያይነት ከዩንቨርስቲዉ ማህበረሰብ በተነሱ አስተያየቶችና ጥያቄዎች ዉይይት ተካሄዶአል፡፡

የዩኒቨርሲቲው ማህበረሰብም በተነሱት ሁለት አበይት ርዕሶች ላይ የተወያዩ ሲሆን በዚህም የተለያዩ ሀሳቦች፣ጥያቄዎችና አስተያየቶች ተንሸራሸረዋል፡፡ በቀጣይም እንደነዚህ አይነት በዓላት በይበልጥ እየተጠናከሩ ቢቀጥሉ የመወያያ መድረኮች ቢዘጋጁናእኛም ሃሳባችንን ብንገልጽ ልዩነቶችን እያጠበብን የምንሄድበትና ችግሮችም ሳይባባሱ በጊዜ መፍትሄ የምናፈላልግበት መድረክ ስለሚሆን ወሳኝ ሚና መጫወት እንችላለን በማለት አስተያየታቸዉን ሰጥተዋል፡፡



## ዶ/ር ተመስገን ቡርቃ
*የዩንቨርሲቲዉ ሥራ አመራር ቦርድ ሰብሳቢ*









# ECSU & EMI Sign MoU

Ethiopian Civil Service University (ECSU) and Ethiopian Management Institute (EMI) signed Memorandum of Understanding (MoU).The agreement is focused on exchanging professionals and sharing resources.



**Prof.Fikre Dessalegne**
*ECSU president*

**W/ro Wubamlak Eshetu**
*EMI Director-General*

The bilateral agreement was signed on 25th November, 2020 at ECSU Senate Hall between Professor Fikre Dessalegne, President of ECSU and w/ro Wubamlak Eshetu, EMI Director-General. Delegated members of both parties attended the MoU signing ceremony.



ECSU president, Professor Fikre Dessalegne, said this agreement enhance the two institutions to share their experts and resources in order to meet their goal effectively.We will have to change the MoU in to action by delegating focal person from the two institutions he underlined.

W/ro Wubamlak Eshetu, EMI Director-General, said we are neighboring institutions and we exchange man power for the last years and now we can make it more formal by signing this MoU. This MoU will help both parties to share resources and facilities. The two institutions are working effectively on training and consultancy services, so we can bring our effort together and make join consultancies and training to address challenges and gaps in different areas. In addition, we can identify and propose further area of cooperation she underscored.





According to the MoU, ECSU and EMI have the desire to:-

- Avail staff to work together on competency-based training, consultancy and research to the public sectors as appropriate
- Share training facilities and accommodations when needs arise and as appropriate
- Share experiences each other for the common good of the public sectors
- Identify and proposes further areas of cooperation

Ethiopian Management Institute (EMI) is a public enterprise that has been operating in Ethiopia as a service provider since 1958.



# Research and Community Service Inaugurates Research Resource Center

Ethiopian Civil Service University, Research and Community Service inaugurated the newly established Research Resource Center on November 26, 2020 at the presences of researchers and academia.



**W/ro Amelework Wube**
*Director for the Library and Documentation Directorate*

On the inauguration program, Dr. Alemayehu Debebe, Vice President of Research and Community Service, welcomed the researchers and academia participated in the program and noted that the center is rich in resources and become available for the academic world in the compound. This shows that the library is coming to us with huge resources instead of we are going to the library. He also stressed the need to use these resources wisely and thanked all individuals who contributed to the establishment of the center.





**Dr. Alemayehu Debebe**
*Vice President of Research and Community Service*

W/ro Amelework Wube, Director for the Library and Documentation Directorate, on her part said that the library has been organized properly with a large electronic resource that researchers, teachers and students in the university compound can access these resources easily. This lessens the effort needed and the time spent to get these materials so far. In order to make these resources available, the university has spent a huge amount of money and it is expected of every researcher and the academic staff to use these resources for their researches as well as teaching learning activities and contribute for the high citation of the university thereby upgrade the university's status in the academic world, W/ro Amelework added.



During the event, it is indicated that ECSU library has 31 subscribed e-journal databases, 55,000 e-books, more than 1,500 e-thesis and dissertations and 6 international online databases connected with ECSU server, and can be access using the local network.

# Mindset Training given to Community Radio Staff

A two-day mindset training was given to Ethiopian Civil Service University FM 100.5 Community Radio staff members from November 17 to 18, 2020 at ECSU Community Radio station. The training was delivered by Dr. Waqgari Negari, Vice President for Training and Consultancy service, and 20 radio station staff members participated in the training.

The main purpose of the training was to enable the members of the station to be aware of and deeply evaluate their current psychological makeup and make out what they should do in the future. The training also helped them to reorganize and develop their potential in more professional manner.





**Dr. Waqgari Negari**
*Vice President for Training and Consultancy service*


The major focus area of the training was issues related to identity, logical thinking, psychological makeup and implementation and approach to different mindset. In addition, the trainer produced proof of detailed explanations based on his life experience and knowledge.



Finally, the trainees were given an assignment to assess their current situation based on the knowledge they acquired during the training time and recreate their plans and activities for the future.







# የ2013ዓ.ም የትምህርት ዘመን መጀመርን አስመልክቶ በፕሮፌሰር ፍቅሬ ደሳለኝ የተላለፈ መልዕክት

**የኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ የኮረና ቫይረስ ወረርሽን መከሰትን ተከትሎ ተቋርጦ የነበረውን የገጽ ለገጽ የመማር ማስተማር ተግባር ተማሪዎችን በዙር በመጥራት የጀመረ መሆኑ ይታወቃል፡፡ ከዚህ ጋር ተያይዞም በቅደመ ቅበላ ዝግጅቱ፣ የትምህርት አሰጣጥ ሂደቱ እና ሌሎች ተዛማጅ ርዕሰ ጉዳዮች ላይ የዩኒቨርሲቲያችን ፕሬዚደንት ፕሮፌሰር ፍቅሬ ደሳለኝ ለተማሪዎችና ለመላው የዩኒቨርሲቲው ማህበረሰብ መልዕክት ያስተላለፉ ሲሆን መልዕክቱን እንደሚከተለው አቅርበነዋል፡፡ መልካም ንባብ፡፡**

የተከበራችሁ ተማሪዎችና መላው የዩኒቨርሲቲው መህበረሰብ በሙሉ ሁላችንም እንደምናውቀው ላለፉት 10 ወራት ዩኒቨርሲቲው የሚሰጠውን ስልጠና እና ትምህርት ተቋርጦ ቆይቷል፡፡ ለዚህም ምክንያት የሆነው የኮቪድ 19 ወረርሽኝ ሲሆን፤ በቅርቡ በሰሜኑ የሀገራችን ክልል በተከሰተው የህግ ማስከበር ስራ ምክንያት ዩኒቨርሲቲው ስራውን



**ፕ/ ር ፍቅሬ ደሳለኝ**

***የኢሲሠዩ ፕሬዚዳንት***

ይጀምራል ብለን ካሰብንበት ቀን በተወሰኑ ቀናት ለማራዘም ብንገደድም በአሁኑ ሰዓት ነገሮች ወደነበሩት በመመለሳቸው አገልግሎቶቹን መልሰን ለመጀመር በቅተናል፡፡ መደበኛውን ስራችንንም መንግስት በሰጠን አቅጣጫ መሰረት ብርቱ ጥንቃቄ አድርገን በስልጠና ስራዎቻችንን የጀመርን ሲሆን በአሁን ሰዓትም የገጽ ለገጽ የመማር ማስተማር ስራችንን ለመጀመር ለተማሪዎች ጥሪ ተደርጎላቸው ወደ ጊቢው ገብተዋል፡፡ በዚህም በጣም ደስተኞች መሆናችንን ለመግለጽ እወዳለሁ ፡፡

በኮቪድ 19 ፕሮቶኮል እና የሳይንስና ከፍተኛ ትምህርት ሚኒስቴር ባስቀመጠው አቅጣጫ መሰረትም አሁን የተቀበልናቸው ተመራቂ ተማሪዎችንና በመጀመሪያ ዲግሪ የሶስተኛ አመት እና ሌሎችም በድህረ ምረቃ በማስተርስና በፒኤችዲ እንዲሁም ነባር ተማሪዎችን ነው፡፡ በተጨማሪም የመጀመሪያ ዲግሪ ሶስተኛ አመት ተማሪዎችንም አካተን ተቀብለናል፡፡

በአጠቃላይ በመደበኛ የትምህርት ፕሮግራም 1750 ተማሪዎችን ተቀብለናል፡፡ በተጨማሪም የዶርሚተሪ (የመኝታ) አገልግሎት የማያገኙ የቅዳሜና እሁድ እንዲሁም የማታ ተማሪዎች ያሉንን ነባርና አዳዲስ ተማሪዎችን ሁሉንም ለመቀበል በቂ ዝግጅት አድርገናል፡፡

ከዚህ አንፃር አሰራራችንንም በአካዳሚክ እና የአስተዳደር አገልግሎት ዘርፍ በሚል በሁለት ከፍለን እየሰራን እንገኛለን ። የአካዳሚክ አገልግሎትን በተመለከተ አዲስ የአካዳሚክ ካላንደር ተዘጋጅቶ በሴኔት ጸድቋል። የዚህ አመት ካላንደር ከወትሮው ለየት የሚያደርገው እንደቀድሞው መርሀ ግብሩ በመስከረም ወር የሚጀመር ሳይሆን ከታህሳስ ወር የሚጀመር መሆኑ ነው። በኮቪድ ምክንያት የባከነውን ያለፈውን ዓመት የትምህርት መርሀ ግብር ለማካካስና የዚህንም ዓመት እቅድ በማካተት ተማሪዎችን ለማስተማር ያስችለን ዘንድ የዓመቱ መርሀ ግብር በሶስት ሴሚስተር ተከፋፍሏል። አንድ ሴሜስተርም ከዚህ ቀደም እንደነበረው በአራት ወራት ሳይሆን ከሁለት እስከ ሁለት ወር ተኩል ድረስ የሚይዝ ሲሆን እስከ ሐምሌ ወር መጨረሻ ባለው ጊዜ ውስጥ ትምህርት ለማጠናቀቅ የተዘጋጀ መርሀ ግብር ይሆናል። በዚህም መምህራንም ሆነ ተማሪዎች ትልቅ ጫና ውስጥ ሊገቡ ይችላሉ። የትምህርት አሰጣጥ ሂደቱም የሚሆነው እንደከዚህ ቀደሙ በገጽ ለገጽ ትምህርት ብቻ ሳይሆን ተማሪዎች በቤታቸው ውስጥ ሆነው መስራት እንዲችሉ ይደረጋል። የተለያዩ ቪዲዮዎችን በማዘጋጀት እንዲማሩባቸው በማድረግና ኦንላይን በመሆን ትምህርታቸውን መከታል እንዲችሉ ታሳቢ ተደርጎ የተዘጋጀ መርሀ ግብር ነው። ከዚህ ጋር ተያይዞም ከኮቪድ 19 ፕሮቶኮልን ተከትለን የትምህርት ክፍለ ጊዜው ላይ ማስተካከያ ያደረግን በመሆኑም ተማሪዎች በአንድ ክፍለ ጊዜ 35 ደቂቃ ብቻ በክፍል ውስጥ እንዲቆዩ ይደረጋል። በአዲሱ ስታንዳርድ መሰረትም በአንድ ክፍል ውስጥ ከ15-20 ተማሪዎችን ብቻ ነው በክፍል ውስጥ ማስተማር እምንችለው።

በክፍል ውስጥ ሊደረጉ የሚገቡ ጥንቃቄዎችን በተመለከተ በተማሪዎች መካከል የሚኖረው ርቀት እና በተማሪዎቹና በመምህራን መካከል የሚኖረው ርቀት በሀገር አቀፍ ደረጃ በወጣው ህግ መሰረት የተደራጀ ነው። ከተማሪዎች የሚጠበቁ ህጎችም አሉ። በመማሪያ ክፍሎች ውስጥ ማስክ ማድረግ ግዴታ ሲሆን ተማሪዎች በመማሪያ ክፍሎች አካባቢ በሚገኙ የእጅ መታጠቢያ ቦታዎች ላይ እየታጠቡ ወደ ክፍላቸው እንዲገቡ ነው የሚጠበቀው። በቤተ-መፅሀፍት ላይ የሚኖረውን ጫና ለማቃለልም የአጋዥ መሳሪያዎችም በዲጂታል ላይብረሪያችን በሚገባ አዘጋጅተናል።

ተማሪዎችም በዚህ ወቅት ከፍተኛ ጥረት ማድረግ ይጠበቅባቸዋል። ይህም ያለው የመማር ማስተማር ሰዓቱ ትንሽ ከመሆኑ አንፃር ጠንክሮ መስራት እና በትኩረት ማጥናት ይጠበቅባቸዋል። በባለፈው ዓመት የሁለተኛ ዲግሪ መርሀ ግብር ትምህርቶችን እና መመዘኛዎችን በኦንላይን ያከናወንን ቢሆንም አንዳንድ ተማሪዎች በሚኖሩበት አካባቢ የኢንተርኔት አገልግሎት ባለማግኘታቸው ምክንያት አንዳንድ ትምህርቶችና ምዘናዎች አምልጠዋቸዋል። ለዚህም አሁን ጉድለታቸውን እያሟሉ እንዲሄዱ የማድረግ ስራ እየሰራን እንገኛለን።

ከመማር ማስተማሩ ሂደት ሌላ ያለውና ሁለተኛው አገልግሎት ደግሞ የአስተዳደር አገልግሎት ሲሆን ይህም የመመገቢያ፣ የመኝታ፣ የክሊኒክ እና የመሳሰሉትን አገልግሎት የሚመለከት ነው። ዩኒቨርሲቲያችን ባለፈው አመት በጊዜያዊ ማቆያነት ተመርጦ አገልግሎት ይሰጥ እንደነበር የሚታወቅ ነው። በማቆያነት ሲያገለግሉ በነበሩት ክፍሎች ላይ በተማሪዎች ዘንድ ምንም አይነት ጥርጣሬ እንዳይኖር ለማድረግ ክፍሎችን የማፅዳትና የፀረ-ተባይ ርጭት ተካሂዷል። ሁሉንም ፍራሽ እና ትራሶች በአዲስ ቀይረናል። ይህም ዩኒቨርሲቲው ማቆያ በነበረበት ወቅት ምንም በበሽታው የተያዘ ሰው ባይኖርም የተማሪዎችን ስጋት ለመቀነስ ታስቦ የተሰራ ነው። በመኝታ ክፍሎች ውስጥም ክፍሎቹ ከዚህ በፊት ከሚይዙት አቅማቸው በግማሽ ቁጥር የቀነሰ ተማሪ እንዲይዙ በማድረግ አደራጅተናቸዋል።

ተማሪዎችም በማንኛውም እንቅስቃሴዎች ንፅህናቸውን እየጠበቁ መንቀሳቀስ ይኖርባቸዋል። ይህም ሲባል ወደ መማሪያ ክፍሎች፣ ቤተ-መጻህፍት ፣ካፌቴሪያ፣ መኝታ ክፍል ሲገቡ እጆቻቸውን መታጠብ ይኖርባቸዋል። በዚህም ወቅት ንክኪዎች እንዳይኖሩ ከእጅ ንክኪ ውጭ የሆኑ የመታጠቢያ መሳሪያዎች አዘጋጅተናል። ሌላው በየቦታው በሚገኙት የሰውነት ሙቀት መለኪያ መሳሪያዎች ሙቀታቸውን እየተለኩ መንቀሳቀስ ይኖርባቸዋል።

በዚህም መሀል የበሽታውን ምልክት የሚያሳይ ተማሪ ቢኖር ለይቶ ማቆያ ቦታ አዘጋጀተናል። ለዚህም በመኝታ ክፍሎች ውስጥ ምልክቶች የታየባቸው ተማሪዎችን በተለያዩ የማስታወቂያ ሰሌዳዎች ላይ የተገለጹ የስልኮች




**ፕ/ ር ፍቅሬ ደሳለኝ**

*የኢሲሱዩ ፕሬዚዳንት*

ቁጥሮችን በመጠቀም ጥቆማውን ማድረግ ይችላሉ። በመመገቢያ አዳራሾችም ላይ ተመሳሳይ የሆኑ ጥንቃቄዎች የሚደረጉ ሲሆን በተወሰነ መልኩ የመመገቢያ ሰዓቶች ማሻሻያ ተደርጎባቸዋል። የዩኒቨርሲቲው ክሊኒክም ከመቼውም ጊዜ በበለጠ ዝግጅት አድርጓል። ከኮቪድ ወረረሽኝ ጋር በተያያዘ ከሚሰሩ ተቋማት ጋርም ትስስሮችን ፈጥሯል።

በሀገር አቀፍ ደረጃ በተቀመጠው አቅጣጫ መሰረት ግብዓቶችን ማለትም ሳኒታይዘር ማስክ እና የመሳሰሉት ግብዓቶች ተቋማት እንዲያቀርቡ የሚል አስገዳጅ ሁኔታ የለም። ነገር ግን ግብዓቶች ከሚያቀርቡ ተቋማት በማምጣትና ለተማሪዎቹ በቅናሽ እንድንሸጥ የተቀመጠ አቅጣጫ ነው ያለው። በመሆኑም ዩኒቨርሲቲያችን ከሌሎች ተቋማት ለየት የሚያደርገው ተማሪዎቹ ሲቪል ሰርቫንት ስለሆኑ በቅናሽ የመጣውን ግብዓት መግዛት ይችላሉ የሚል እምነት ነው ያለን።

የመማር ማስተማሩ ተግባር በታቀደው መሰረት እንዲከናወንም አመራሮች የአመራር ስራቸውን በአግባቡ ሊወጡ ይገባል:: በተዘጋጀው መርሀ ግብር መሰረት እንዲፈፀሙ የአስተዳደር ዘርፉ ከፍተኛ ስራ ይሰራል። ከመምህራን አንፃር መምህራን ዋናውን የመማር ማስተማር ስራን በበላይት የሚመሩ እንደመሆናቸው መጠን በወጣው የአጭር ጊዜ ሰሌዳ የተለያዩ የማስተማሪያ ዘዴዎች ተጠቅመው ውጤታማ የሆኑ ተማሪዎች እንዲያበቁ ይጠበቅበቸዋል። የድጋፍ ሰጪ፣ የምግብ አገልግሎት የሚሰጡት አካላት ሁሉም የየራሳቸውን ሚና ስርዓቱን በጠበቀ መልኩ መወጣት ይኖርባቸዋል።

በአጠቃላይ እስከአሁን ተባብረን በመስራታችን አሁን እስካለንበት ደረጃ የተለያዩ ውጤቶችን እያስመዘገብን መጥተናል። ለቀጣይም በወረርሽኙ እና በፀጥታ ማጣት ምክንያት የተስተጓጎሉ ስራዎቻችንን በብቃት ፈፅመን በዓመቱ መጨረሻ ላይም ይህንን የምንዘክርበት እንዲሆን በጋራ ተባብረን እንስራ ስል መልዕክቴን አስተላልፋለው።

አመሰግናለሁ።

# 15ኛው የብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች በዓል አከባበር በኢ.ሲ.ሰ.ዩ



የኢትዮጵያ ብሔር ብሔረሰቦች እና ህዝቦች የጋራ የቃል ኪዳን ሰነዳቸው የሆነውን ህገ መንግስት ያጸደቁበትን ህዳር 29 ቀን በየዓመቱ የኢትዮጵያ የብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ቀን በማለት ይከበራል፡፡ በዓሉም ዘንድሮ ለ 15ኛው ጊዜ በመላው ሀገሪቷ **"እኩልነትና ህብረ ብሔራዊ አንድነት ለጋራ ብልጽግና"** በሚል መሪ ቃል በተለያዩ ስነ ስርዓቶች የተከበረ ሲሆን በኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲም ህዳር 22 እና 23 ቀን 2013 ዓ.ም መላው የዩኒቨርሲቲው ማህበረሰብ በሳተፉበትና በዩኒቨርሲቲው ምሁራን ለዉይይት መነሻነት በቀረቡ ሁለት ጽሁፎች ላይ በተደረገ የውይይት መርሀግብር ተከብሮ ውሏል፡፡

በውይይቱ መክፈቻ ላይ ፕሮፌሰር ፍቅሬ ደሳለኝ ባደረጉት የእንኳን ደህና መጣችሁ ንግግር ኢትዮጵያ ሀገራችን በበርካታ ብሔር ብሔረሰቦች የተገነባች በየዘመናቱ ያጋጠሟትን ችግሮችም በልጆቿ ህብረትና አንድነት እያለፈች እዚህ የደረሰች ሀገር መሆኗን አስታውሰው ዛሬም በሰሜኑ የአገራችን ክፍል መንግስት ህግን የማስከበር ስራ እየሰራ እንደሚገኝ ገልጸዋል፡፡ ህግ የማስከበሩ ስራ እንዳለ ሆኖ ችግሮችን በሰለጠነ መንገድ በንግግርና በጠረጴዛ ዙርያ የመፍታት ባህላችን የዳበረ ባለመሆኑ ትልቅ ዋጋ እየከፈልን እንገኛለን ያሉት ፕሮፌሰር ፍቅሬ አንድነታችንን የሚያጠናክሩና የጋራ እሴቶቻችንን እንደገነባነው ሁሉ ከዚህ በተቃራኒ ወቅት እየጠበቁ የሚከሰቱ ግጭቶችና ጦርነቶች የተማረውንና አምራች ኃይል እያሳጣን እንዲሁም ባለን ውሱን ሀብት የተገነቡ መሰረተ ልማቶችን እያወደመ፤ የህዝቦችን የእርስ በርስ ግንኙነት እያሻከረ ከድህነት አዙሪት እንዳንላቀቅ አድርጎናል፡፡ ከዚህ አዙሪት ለመውጣት ምሁራን የመፍትሔ ሀሳብ የሚያመላክት ውይይት በማድረግ ያለብንን ሀገራዊ ኃላፊነት መወጣት ይገባናል ሲሉ መልዕክታቸውን አስተላልፈዋል፡፡

በበዓሉ ላይም **"ሀገራዊ ለውጥ ለጠንካራ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ስርዓት ግንባታ"** እና " ወቅታዊ ሀገራዊ ጉዳዮች" በሚሉ ሁለት ርዕሰ ጉዳዮች ላይ የተጠናቀሩ ጽሑፎች በዶ/ ር አለማየሁ ደበበ እና በዶ/ር ዋቅጋሪ ነጋሪ አማካይነት ለውይይት ቀርበዋል፡፡ ሀገራዊ ለውጥ ለጠንካራ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ስርዓት ግንባታ በሚል ርዕስ በቀረበው ጽሑፍ ላይም የምንፈልጋት ኢትዮጵያ ዘላቂ ሰላም ፣ ዴሞክራሲ፣ ፍትህ እኩልነትና ወንድማማችነት እንዲሁም ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ እድገት የሰፈነባት ሀገር መሆኗንና ለዚህም የሁሉም ማህበረሰብ ርብርብና ትብብር እጅግ ወሳኝ መሆኑ ተገልጿል፡፡ በጽሑፉ ላይም ከሀገረ መንግስት ግንባታ፣ ከብሔረ መንግስት ግንባታና ከዲሞክራሲያዊ ስርዓት ግንባታ አንጻር ሀገራችን ምን እንደምትመስል በስፋት የተብራራ ሲሆን መዋቅራዊ ለውጥ እንደ ህልውና ጥያቄ መታየት እንዳለባቸውና የሚሰሩ ስራዎችም ዘመን ተሻጋሪ ሊሆኑ እንደሚገባ ተመላክቷል፡፡

በሀገራዊ ወቅታዊ ጉዳዮች በተለይ የፌዴራል ስርዓቱን ለማዳን የተከናወኑ ተግባራትእና ኢ-ህገመንግስታዊ እንቅስቃሴ ከፌዴራል ስርዓት አንጻር ያለውን አንድምታና ከለውጡ ማግስት ጀምሮ ለውጡን ለማደናቀፍ የተደረጉ እንቅስቃሴዎች በዝርዝር የቀረቡ ሲሆን ከመወያያ ርዕሶቹ ጋር ተያይዞ ከበአሉ ተሳታፊዎች በርከት ያሉ ሀሳብና አስተያየቶች ቀርበዋል፡፡

ተሳታፊዎቹ በሰጡት አስተያየትም በዓሉ ህገ መንግስቱ የጸደቀበትን ቀን መሰረት አድርጎ የሚከበር በመሆኑም መነሻችንን ፍቅር አድርገን፣ ከበዳይና የተበዳይ ትርክት በመውጣት በአሉን በወንድማማችነት መንፈስ ማክበር ተገቢ መሆኑ ተገልጿል፡፡ ህገ-መንግስቱን አስመልክቶ ለብዙ ችግሮች መንስኤና ለተለያዩ የእርስ በርስ ግጭቶችም መንገድ ከፍቶአል የተባሉ አንዳንድ አንቀጾቹ ሁሉንም ህብረተሰብ በማሳተፍ ሊሻሻሉ እንደሚገባ ፤ በዚህ ዘመን ኢትዮጵያ ውስጥ ያለው የብሔር ተኮር ፖለቲካ የዜጎችን በፈለጉበት ክልል ተንቀሳቅሰው የመስራት መብትን አደጋ ላይ የጣለ በመሆኑና ይህ አካሄድ ለማንም የማይጠቅም፣ መከፋፈልንና መተራረድን ያስከተለ በመሆኑ መስተካከል እንደሚገባው አጽንኦት በመስጠት አመላክተዋል፡፡

የፖለቲካ ፓርቲዎችም አደረጃጀቶቻ ፕሮግራሞቻቸው ተፈትሸው ህብረ ብሔራዊነትን መላበስ እንደሚገባቸው የገለጹት አስተያየት ሰጪዎቹ ለአንድ ብሔር መወገንና ሁሉን አካታች ያልሆነ አደረጃጀት ይዞ ሀገርን ለመምራት መንቀሳቀስ ሀገራችንን ወደ ፋሽስታዊ አካሄድ የሚመራ መሆኑን በቅርቡ ከተከሰተው ድርጊት በመማር ይህን አካሄድ ማስወገድ ተገቢ ነው ብለዋል፡፡

እንደ ከፍተኛ የትምህርት ተቋምም የኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ ምሁራን በሀገረ መንግስትም ሆነ በብሔረ መንግስት ግንባታው እንዲሁም የዲሞክራሲያዊ ስርዓት ግንባታውን የሚያግዙ ፤ በየቦታው ለሚከሰቱ ግጭቶችና ተያያዥ ችግሮች መፍትሔ የሚያመላክቱ ጥናቶችንና ምርምሮችን ምሁራዊ ተልዕኮን በመውሰድ መስራትና ማቅረብ ተገቢ መሆኑንና ለዚህም የራሳቸውን ሚና መጫወት እንዳለባቸው ገልጸዋል፡፡ አያይዘውም በብሔር ተደራጅቶ መታገል የብሔርን ነፃነት የሚያረጋግጥና የብሔር ብሔረሰቦችን መብት ማስከበር የሚያስችል ስለመሆኑ በደንብ በጥናት ሊፈተሽ የሚገባ ጉዳይ ሊሆን እንደሚገባ ተናግረዋል፡፡

ኢትዮጵያ ውስጥ በነበረው ስርዓት በሶስቱ የመንግስት ተቋማት ማለትም በህግ አውጪው፣ ህግ ተርጓሚውና በህግ አስፈጻሚው መካከል ውጤታማ የሆነ የቁጥጥር ስርዓት /check and Balance / እንዳይኖር እና ተቋማት በሙሉ የፖለቲካ ስርዓቱ አገልጋይ እንዲሆኑ መደረጉን ያወሱት ታዳሚያኑ በአሁን ወቅት የመጣውን ለውጥ ተከትሎ ዘላቂና ቀጣይ የሆኑ በራሳቸው የሚንቀሳቀሱ /autonomous/ የሆኑ ተቋማትን መገንባት እንደሚገባ አስምረውበታል፡፡ ተቋማትን መገንባት ብቻ ሳይሆን ተቋማትን የሚመሩ ኃላፊዎችም የአገልጋይነት መንፈስ ሊላበሱ እንደሚገባ፤ ነፃ ገለልተኛና ብቃት ያለው ተቋማት ግንባታ እጅግ በጣም ወሳኝ መሆኑ ተጠቅሷል፡፡ ቀደም ሲል የነበሩት በተለይ ጸረ ሙስና ፣ የእንባ ጠባቂ፣ ሰብአዊ መብት ወዘተ. የመሳሰሉት ተቋማት የፖለቲካ ስርዓቱ አገልጋይ ነበሩ ለማለት ይቻላል፡፡ ትላልቅ ሙስናዎችን የማይነኩ በተቃራኒዉ ትንንሽ ሙስናዎችን የሚያሳድዱ ነበሩ፡፡ እነዚህ አሰራሮች ካልተለወጡ ለውጥ የሚባለው ነገር ትርጉም አይኖረውም፤ ፍትህ በትክክል የማይገኝበትና ወንጀለኛ ከሀገር እስኪወጣ ድረስ ሽፋንና ከለላ የማይሰጥ ተቋም መገንባት ያስፈልጋልም ብለዋል፡፡

ከወቅታዊ ጉዳዮች ጋር በተያያዘም መንግስት ህግን ለማስከበር እየሰራ ያለው ስራም ተገቢ መሆኑን የገለጹትየበአሉተሳታፊዎችለመከላከያሰራዊታችን ያላቸውን ክብርና አድናቆትም ገልጸዋል፡፡ በየክልሉ አስተዳደር ውስጥ ተሰግስገው አሁን ደግሞ እንደጀግና የለውጥ ሀዋርያ መስለው የሚታዩ አካላት መታደንና መጠየቅ እንደሚገባቸው ታዳምያኑ አስተያየታቸውን ለግሰዋል፡፡

የሀገራችን የትምህርት ስርዓትም ኢትዮጵያን እንደ ኢትዮጵያ የማያውቃትና በክልሉ ላይ ብቻ የታጠረ ትውልድ እያፈራ በመሆኑ የኢትዮጵያውያን የጋራ ታሪክ የሚያውቅ ትውልድ መፍጠር ባለማስቻሉ ይህ ጉዳይ በአግባቡ በምሁራን ተጠንቶ በትምህርት አገራችንን ለማሳደግ ክለሳ ሊደረግበት እንደሚገባ አስተያየት ሰጪዎቹ ጠቁመዋል፡፡ በየክልሉ የተከማቸ ልዩ ኃይልን አስመልክቶም ለወደፊቱም በየክልሉ የሚቋቋሙ ልዩ ኃይል የሚባለው ስልጠና እና የአካባቢ ልዩ ኃይል የሚቀርበት ሁኔታ ቢፈጠርና

በሀገር ደረጃ የሚቋቋምበት መንገድ ቢታሰብበት መልካም መሆኑ ተጠቁሟል፡፡

የህግ የበላይነት ጋር በተያያዘም ከቃል ባለፈ በተግባር ሊገለፅ ይገባል ያሉት አስተያየት ሰጪዎች ከህግ ውጪ የተሰሩ ስራዎችም በቀጣይነት እንዳይደገሙ መሰራት አለበት ብለዋል፡፡ አሁን ያለውን ሁኔታ ስንመለከት በታችኛው እርከን ላይ ያሉት ሰራተኞች በየወረዳው ህዝቡን እያማረሩት ያሉበት ሁኔታ ስላለ ሳይቃጠል በቅጠል እንዲሉ መንግስት ቢመለከተው መልካም መሆኑን የተገለጸ ሲሆን ከመድረኩ በተሰጠ ምላሽ የመልካም አስተዳደር ችግር በአዲስ አበባ ብቻ ሳይሆን በየክልሉ በርካታ ችግሮች ያሉበት መሆኑ ተጠቅሶ በአሁኑ ወቅት ሀገሪቱ በለውጥ ላይ ከመሆኗ እና ካለመረጋጋቱ ጋር ተያይዞ የሚታዩትን ችግሮች በመገንዘብ ችግሩን ለመቅረፍ የሁሉም ተሳትፎ እጅግ አስፈላጊ መሆኑ ተገጿል፡፡

ባለፉት 27 አመታት የሰራነውም በስፋት ልዩነታችን ላይ ሲሆን በጋራ እሴቶቻችን ላይ ስራዎች ባለመሰራታቸው የጋራ እሴቶቻችን በከፍተኛ ሁኔታ መሸርሸራቸው ከፍተኛ የሆነ ችግር አስከትሏል፡፡ ስለዚህም ሀገራዊ አንድነትና ብሔራዊ ማንነትን በሚዛንነት ይዘን የምንሄድበትን በጥናት ለይቶ መስራትና በዚህ መሰረት ወደፊት መጓዝ እንደሚገባም በውይይቱ የተመላከተ ሲሆን መሻሻል የሚገባውና መቀየር ያለበትን ጉዳይ መለየትና የጋራ እሴቶቻችንን የምናዳብርበት መንገድ መለየት እንጂ ያለውን ነገር በሙሉ አስወግዶ አዲስ ነገር ለማምጣት መቻኮልም ተገቢ አለመሆኑና አዲስ ስርዓት በመጣ ቁጥር የነበረውን እንዳለ የማስወገድ አካሄድ መውጣት እንደሚገባ ከመድረኩ ተገልጿል፡፡

በአጠቃላይ ከተሳታፊዎች ለተነሱት ጥያቄዎችን አስተያየቶች ላይ ከመድረኩ የተለያዩ ግብረ መልሶች የተሰጡ ሲሆን ከተሰጡት ምላሾች መካከልም በአገራችን ቀደም ሲል ህገ መንግስት ቢኖረንም በህገ መንግስታዊነት ስርዓት እየተመራን አልነበርንም የሚለው ይገኝበታል፡፡ ህገ መንግስቱ ላይ የተቀመጡ ነገሮች እንኳን በአግባቡ ተግባራዊ እየተደረጉ አይደለም፡፡ በህገ መንግስቱ መሰረት ብሔር ብሔረሰቦች በሀገራቸው ውስጥ በማንኛውም የኢትዮጵያ ክፍል ተንቀሳቅሰው እንዲሰሩ ይፈቅዳል፡፡ ነገር ግን በሁሉም ክልል መፈናቀል ይታያል፡፡ ሌላው በህገ መንግስቱ የሀገር መከላከያ ሠራዊት ገለልተኛና የሀገርን ሉአላዊነት የሚያስጠብቅ መሆኑ ተቀምጧል፡፡ ነገር ግን አብዮታዊ ዲሞክራሲ ግን ሰራዊቱን የፓርቲ ጠባቂ እንዳደረገውና ለዚህም ሰራዊቱ ውስጥ ያለውን ከፍተኛ አመራር ከአንድ ቡድን መሆኑና በሰሜን እዝ ላይ የተፈጸመው ጥቃት ጥሩ ማሳያ መሆኑ ተገልጿል፡፡ ስለዚህ ነጻና ገለልተኛ ተቋማትን መመስረት አስፈላጊ መሆኑና ይህ ደግሞ በሰዎች አዕምሮ ላይ የሚሰራ እንደሆነ ተገልጿል፡፡

የፌደራል ስርዓቱ በተመለከተ ብሔሮችና ብሔረሰቦች የነጻነት ትግልን ተከትሎ ራሳቸውን እንዲያስተዳድሩ የተመሰረተ በመሆኑ ብሔር ብሄረሰቦች ራሳቸውን አስተዳድረዋል፡፡ የተለያዩ የማይታወቁ ብሔር ብሔረሰቦች ባህላቸውንና ቋንቋቸውን አሳድገዋል፡፡ ነገር ግን ስርዓቱ ወደመሬት ሲወርድ ሁሉም አካል በራስ ቡድንና ጎጥ አልፎም በግል ጥቅሙ ላይ በመጠመዱና ኢ-ፍትሀዊ የሆነ የሀብት ክፍፍል በመንሰራፋቱ የእውነተኛ ፌደራሊዝም አለመተግበር፤ ስርዓቱ ለመበስበስና ለመውደቅ መብቃቱና ችግሮቹም በስፋት መታየታቸው የተጠቀሰ ሲሆን ለወደፊቱ “በምን አይነት ስርዓት እንመራና በምን አይነት አደረጃጀት እንደራጅ?” የሚለው ግን ጥናትን የሚፈልግና ቁጭ ብሎ በመነጋገር ላይ የተመሰረተ በህዝቡ ፍላጎትና ምርጫ ላይ የሚመሰረት መሆን ያለበት ጉዳይ መሆኑ ተመላክቷል፡፡ በአብላጫ ሀሳብ በውይይት እንጂ የእኔ አውቅልሀለው አስተሳሰብ ከዚህ በኋላ የሚያስኬድ ባለመሆኑ በዚህ ጉዳይ ያለ አስተሳሰብና አመለካከት መጀመሪያ መቀየርና መለወጥ እንደሚኖርበት፤ ሁሉም ሀሳብ ወደመድረክ መጥቶ መወያየት መተቸትና የተሻለውም በመቀበል ላይ በተመሰረተ አካሄድ መመራት እንደሚገባ ተገልጿል፡፡

# 15 ኛው የኢትዮጲያ ብሔር ብሄረሰቦችና ሕዝቦች ቀን አከባበር በኢ.ሲ.ሰ.ዩ

## ከ23/3/2013-24/3/2013 ዓ.ም በአባይ አዳራሽ

















## International and Public Relations Coordination Directorate

**Contact Address:**

Tel.0116 46 2887,Extension: 253/252/257 , Fax: 0116463016

P.O.Box5648, E-mail: www.lprd @ecsu.edu.et ,

Website: www.ecsu.edu.et, Tweeter: @ECSU tweets ,FM Radio:-100.5MHz

Facebook: Ethiopian Civil Service University





BUILDING CAPACITIES IN PUBLIC SECTOR SINCE 1995


**PRINTED BY** *International & Public Relations Directorate*